# የአቶ መንግስቱ ዋሲሁን ቢሰጠኝ አጭር የህይወት ታሪክ

አቶ መንግስቱ ዋሲሁን ከአባታቸው ከአቶ ዋሲሁን ቢሰጠኝ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ውቢት ፋንታ በ1954 ዓ.ም በወሎ ክ/ሀገር ዋግ አውራጃ ሰቆጣ ከተማ ተወለዱ::

ከ1961 - 1968 ዓ.ም ከ1ኛ-8ኛ ክፍል የኤለሜንታሪ ትምህርታቸውን በዋግ ስዩም አድማሱ ወሰን ትምህርት ቤት ተከታተሉ::

ከ1969 - 1971 ዓ.ም ባለው ጊዜ በሰሜን ጎንደር ገጠራማ ቦታዎች በመዘዋወር በጸረ ደርግ ትግሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል::

ከ1972 - 1975 ዓ.ም ያለውን ጊዜ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በምስራቅ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ::

በዚህም ከፍተኛ ነጥብ በማምጣት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተሸጋገሩ:: በመሆኑም ከ1976 - 1980 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህግ ፋኩልቲ በመግባት ትምህርታቸውን ጨርሰው በ 1980 ዓ.ም በከፍተኛ ውጤት የህግ ዲግሪ (L.L.B.) አግኝተዋል::

ከ1981 - 1988 ዓ.ም በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት (ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት) የህግ ኤክስፐርት በመሆን አገልግለዋል::

ከ 1989 -1990 ዓ.ም ድረስ በግል የጥብቅና ስራ ተሰማርተው ለወገኖች የህግ ምክርና አገልግሎት ሰጥተዋል::

በሚያዝያ ወር 1990 ዓ.ም በወቅቱ በተፈጠረባቸው ችግር ምክንያት እጅግ ከሚወዷት አገራቸው ኢትዮጵያ በመውጣት ወደ ኬኒያ በስደት ሄዱ::